የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች

# ቋሚ ኮሚቴ

# የ2014 በጀት አመት እቅድ

ህዳር 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

**ማዉጫ** **ገጽ**


መግቢያ----------------------------------------------------------------------------------------------------------4

ክፍል አንድ----------------------------------------------------------------------------------------------------------6

የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ሁኔታዎች------------------------------------------------------6

1. ሀገራዊ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ለቋሚ ኮሚቴው ያላቸው አንድምታዎች------------------------------------------------------------------------------------6

1.1 የሀገራችን ፖለቲካ ሁኔታ---------------------------------------------------------------------------6

1.2 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ--------------------------------------------------------------------------------7

1.3. ማህበራዊ ሁኔታ-----------------------------------------------------------------------------------7

1.4. የጤና፤ ማህበራዊ ልማት፤ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሁኔታ---------------------8

1.5. የመረጠን ህዝብ ከቋሚ ኮሚቴው የሚጠብቃቸው ጉዳዮች እንደመነሻ ተወስዷል-------------8

1.6. የምክር ቤቱ የ5 አመት ስትራቴጂክ እቅድ እንደመነሻ ተወስዷል-------------------------------9

1.7. የምክር ቤቱ የ2014 በጀት አመት እቅድ እንደመነሻ ተወስዷል----------------------------------9

1.8. የ2013 በጀት አመት የቋሚ ኮሚቴው እቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ ተወስዷል---------------10

1.8.1. የአቅም ግንባታ ስራዎች እንደ መነሻ ተወስዷል-------------------------------------------10

1.8.2. የህግ አወጣጥ ተግባራት እንደ መነሻ ተወስዷል-------------------------------------------10

1.8.3. የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት እንደ መነሻ ተወስዷል-------------------------------------11

1.8.4. የመልካም አስተዳደር ስራዎች እንደ መነሻ ተወስዷል-------------------------------------11

1.8.5. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ተግባራት እንደ መነሻ ተወስዷል---------------------------------12

1.9. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም እንደ መነሻ ተወስዷል--------------------------------------------------------------------------------12

1.10. የቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች--------------12

1.11. የአስፈፃሚ አካላት የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች እንደመነሻ ተወስዷል--------------------------------------------------------------13

1.12. በቋሚ ኮሚቴው የሚገኙ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች በ2013 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንደ መነሻ ተወስዷል----------------------------14

1.13. የመነሻ ሁኔታ ማጠቃለያ-------------------------------------------------------------------------16

ክፍል ሁለት-------------------------------------------------------------------------------------------17
2. የ2014 በጀት አመት እቅድ--------------------------------------------------------------------------17
2.1. ቁልፍ ችግር------------------------------------------------------------------------------------17
2.2. ቁልፍ ተግባር----------------------------------------------------------------------------------17
2.3. የእቅዱ ዋና ዓላማ-----------------------------------------------------------------------------17
2.4. የዕቅዱ ግቦችና ዓላማ--------------------------------------------------------------------------18
2.4.1. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች----------------------------------------------18
2.4.2. የ2014 እቅድ ዝርዝር አፈጻጸም-----------------------------------------------------------18
2.5. በዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት-------------------------------------------19
2.6. የተግባር ምእራፍ (ከህዳር -ግንቦት)----------------------------------------------------------20
2.6.1. አቅም ግንባታ-------------------------------------------------------------------------------20
2.6.2. የህግ ማውጣት ግብና ዋና ዋና ተግባራት-----------------------------------------------21
2.6.3. የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ግብና ዋና ዋና ተግባራት-----------------------------------22
2.6.3.1 የአስፈፃሚ አካላትን ሪፖርት መገምገም-----------------------------------------------23
2.6.4 የመስክ ምልከታ ተግባራት--------------------------------------------------------------------25
2.6.4.1. መደበኛ የመስክ ምልከታ---------------------------------------------------------------25
2.6.4.2. መደበኛ ያልሆነ (ድንገተኛ) የመስክ ምልከታ---------------------------------------------27
2.7. በማጠቃለያ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት-----------------------------------------------------32
2.7.1.ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የማጠቃለያ ግምገማ ማካሄድ------------------------------------------------------------------------------------------32
2.7.2.በአፈፃፀም ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች-------------------------------------------------------------------------------------------------33
2.8. የጊዜ ሰሌዳ------------------------------------------------------------------------------------34
ሠንጠረዥ 1. የቋሚ ኮሚቴ የዝግጅት ምዕራፍ------------------------------------------------------36
ሰንጠረዥ 2. መደበኛ የመስክ ምልከታን በሚመለከት የጊዜ ሰሌዳ-------------------------------------37
ሰንጠረዥ 3. የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና የተለያዩ ስልጠናዎች------------------------------38
ሰንጠረዥ 4. በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ ተቋማት ሪፖርት በአካል የሚያቀርቡበት ኘሮግራም------------------40
ሰንጠረዥ 5. በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚያቀረቡ አስፈፃሚ አካላት--------------------------------41

## መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የፓርላሜንታዊ ስርአት መተግብር ከተጀመረ ብዙ ዓመታት የተቆጠረ ሲሆን ይህንንም ተግባር ለማሳለጥ በህግ አውጪ፤ በህግ አስፈፃሚ እና በህግ ተርጓሚው አካላት ተሰይመው በህገመንግስቱ የተሰጣቸዉን ስልጣንና ሀላፊነታቸዉን የሚወጡበት ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርአት ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ፤ ዴሞክራሲን ከማጎልበት አንፃር ሲታይ ቀጥተኛ የዲሞክራሲ ቁልፍ መገለጫ የሆኑት ም/ቤቶች ናቸው፡፡ ምክር ቤቶች በቀጥታ በህዝብ የተወከሉ በመሆኑ የህዝብን የልማት፤ የዴሞክራሲ፤ የፍትሀዊ ተጠቃሚነትን፤ የመልካም አስተዳደር አፈፃፀሞችን እየተከታተሉ ችግራቸውን ለመፍታት የሚያስችል ተልዕኮ ይዘው የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 54 መሰረት በየ5 ዓመቱ ምርጫ እንደሚደረግ የተደነገገ ቢሆንም 6ኛ ዙር የምርጫ ዘመን በኮቪድ 19 ምክንያት በርካታ ተግባራት እንደተቋረጡ ሁሉ የምርጫ ጊዜውንም ማራዘም አስፈላጊ ስለነበርና ይህን ተከትሎ በ2013 ዓ.ም ሰኔ ላይ 6ኛው ዙር ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ተደርጓል፡፡ ምርጫው የኢትዮጲያን ህዝብ የዴሞክራሲ ባህሉን እንዲያጎለብት ከመቼውም በበለጠ ፍታዊ፤ ነፃና ገለልተኛ በመሆን ተፎካካሪ ፓርቲዎችም የተወከሉበት ምርጫ ዘመን ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ምክር ቤቱን በተለይም ቋሚ ኮሜቴውን ይበልጥ ጠንካራ ስራ እንዲሰራ የሚያደርግ ሁኔታ ነው፡፡

አዲሱ የምክር ቤት አባላት ከነባሩ ምክር ቤት በጠንካራ ጎን የታዩትን እንደ መልካም ተሞክሮ በመውሰድ እጥረቶችን በመቅረፍ በህገ-መንግስቱ የተሰጠውን ተግባር ህግ የማውጣት፤ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ፤ የሕዝብ ውክልና መወጣት እና የዲፕሎማሲ ስራ በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመራ የሚያደርግ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በትክክለኛው መንገድ እንዲተገበር እና ተጠያቂነትን ለማስፈን ም/ቤቶች ጠንካራ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ነፃና ገለልተኛ ታማኝ ለእውነትና ለህዝብ የቆመ ስራ መስራት፣ የመረጣቸውን ህዝብ አፍና ጆሮ በመሆን ኢትዮጲያዊ መንፈስ በመያዝ ያለአድሎ በቅንነትና በታማኝነት ለማገልገል የግድ የሚልበት ሁኔታ የተፈጠረ ነው፡፡

በመሆኑም የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሀላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው የአሰራር ስርአት ቋሚ ኮሜቴዎችን ማደራጀት ቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 55 እና በምክር ቤቱ የዉሳኔ ቁጥር 3/20014 የተሰጠውን ተልኮ ለማከናወን ምክር ቤቱ በአዲስ መልክ ካቋቋማቸው 11 ቋሚ ኮሚቴዎች መካከል አንዱ የጤና፤ የማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን 3 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችንና 16 ተጠሪ ተቋማትን ይከታተላል፡፡ እነሱም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ሚኒስቴር፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስተርና ለእነርሱ ተጠሪ የሆኑት ተቋማት ናቸው፡፡

ስለሆነም ቋሚ ኮሚቴው የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በ3 ንኡሳን ኮሚቴዎች ማለትም የጤና፤የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች እና የባህልና ስፖርት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴዎችን በማደራጀት እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ እቅዱ የያዛቸው ዋና ዋና ጉዳዮችን እንደ መነሻ ሁኔታ በመውሰድ የ2013 በጀት ዓመት የቋሚ ኮሚቴው እቅድ አፈፃፀም እንደመነሻ በመውሰድ፣ ሀገራዊ ሁኔታውን፤የባለፈው ምክር ቤት የፈጸማቸውን ሥራዎች፤ የ6 አመት ጉዞ አፈጻጸሞችንና የአዲሱን ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሁኔታዎችን በመዳሰስ የ2014 ግቦችና አላማዎችን አካቶ እንደሚከተለው አዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ሁኔታዎች

## 1. ሀገራዊ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ለቋሚ ኮሚቴው ያላቸው እንድምታዎች

## 1.1 የሀገራችን ፖለቲካ ሁኔታ

ኢትዮጵያ በዚህ 3 ዓመት ውስጥ የዜጎችን ህልውና ለመልማትና ለመበልጸግ የሚያስችል እስትራቴጅ በመንደፍ በለውጥ ጎዳና ላይ ትገኛለች፡፡ ይህን ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ትግልና መስዋትነት የተከፈለበት በመሆኑ ህዝቡ ለውጡን ለማጣጣምና ለማስቀጠል በከፍተኛ ፍላጎት እና ተነሳሽነት መሆኑን ያየበት ነዉ፡፡ ባለፉት አመታት የደረሰበትን የዴሞክራሲ ምህዳር መጥበብ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ሀገሪቱ ወደ አንድነት ከማምጣት ይልቅ የመበታተን አደጋ ተጋርጦበት የነበረውን ስርአት በመቀየር ወደ ተሻለ የለውጥ ምህዋር ውስጥ ለማስገባት ጥረት ተደርጓል፡፡ በህገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ የተቀመጠው አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ እንፈጥራለን የሚለው አስተሳሰብ በተግባር ባለመተግበሩ የመጣዉን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ስራዎችን ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ለበርካታ ዓመታት የተከማቹ ችግሮች በአንድ ጀምበር የማይቀየር አስተሳሰብ በመኖሩ አንድነትን፣ እኩልነትን፤ ወንድማማችነትን፤ፍቅርና ሰላም ያለው ዜጋ በመገንባት ረገድ ውስንነት ስለነበር አሁን ለደረስንበት ሁኔታ አብቅቶናል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም ፍቅር፤ እኩልነት ወንድማማችነትን በማስፈን ከአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነች ሀገር እንፈጥራለን በሚል ስርዓቱ ሪፎርም መደረጉ የግድ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ለዉጥ ያልተዋጠላቸው እኛ ያልገዛናት እኛ እንደፈለግን ያላደረግናት ሀገር ትበተን በማለት አሸባሪዉ ህወሀትና ሸኔ ዛሬ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ እየታተሩ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ወቅት የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ታዉጆ እየተገበርን እንገኛለን፡፡ የኢትዮጲያ ህዝብ በዚህ ሳይበገር በአስተሳሰብ አንድ የመሆን የመተሳሰር ያንዱ ጉዳት ለሌላው ጉዳት ነው በሚል የተቃጣብንን ጦርነት ለመመከት ሁሉም ህዝብ የህልውና ዘመቻ ንቅናቄ ውስጥ ነው፡፡ በተለይም በአማራና በአፋር፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በተደረገው ጦርነት ህይወታቸው የተሰዉ፣ አካላቸው የተጎዱ

ዜጎች፤ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ፤ ህፃናት፣ ሴቶች፣ አረጋዊያንና ወጣቶች እንደዚሁም ፆታዊ ጥቃትና መደፈር የደረሰባቸዉ ሴቶች በርካታ በመሆናቸው ለተወካዮች ም/ቤት አባላትም ይሁን ለመንግስት በጣም ከባድ በመሆኑ ይህ ቋሚ ኮሚቴ በአስተዉሎ መስራት የሚጠበቅበት ነው። እነዚህ ዉስብስብ የሆኑ ማህበራዊ ችግሮች በዚህ ቋሚ ኮሚቴ ሥር የሚታዩ በመሆናቸዉ ሁለገብ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን እና አገራዊ ልማትን ለማሳለጥ ቋሚ ኮሚቴዉ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል።

## 1.2. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተለይም በግብርናና በሌሎች ዘርፎች የሚሰራው ሥራ የሚያበረታታ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ምቹ ሁኔታ ለውጥ በሚያመጣ መንገድ አዳዲስ ስራዎች እየፈጠሩ በመስራት ላይ መሆኑ እና የ10 ዓመት እስትራቴጂክ ዕቅድ ተነድፎለት መነሻ እና መድረሻው ታውቆ እየተሰራ ያለው ኢትዮጲያ ካስቀመጠችው ራእይ የሚያደርስና ትውልድን የሚያሻግር ነው። አሁንም ቢሆን ግብርና እና ኢንደስትሪ በተለይም ማንፋክቸርንግ እና ቱሪዝም ሰርቪስ ሴክተር ላይ አትኩሮ በመስራት ውጤት ለማምጣት እየተሰራ ያለው ሥራ መልካም ቢሆንም አሁን ሥራ መልካም ቢሆንም አሁንም በአሸባሪዉ ህወሀትና ሸኔ የተቃጣብን ወረራ የሰው ኃብታችን አምራቹን ወጣት እና ኢኮኖሚውን የሚያደቅና የሚበላ በመሆኑ በፈለግነው ፈጥነን ለመሄድ እንቅፋት በመሆኑ ቋሚ ኮሚቴው ይህን አውቆ መስራት የሚገባን ወቅት ላይ በመሆኑ ይህን ተረድቶ መዘጋጀት እንዳለበት ያመላክታል።

### 1.3. ማህበራዊ ሁኔታ

በማህበራዊ ሁኔታችን ያመጣናቸውን ለውጦች እንዴት መከላከልና መቆጣጠር እንደምንችል ተሞክሮ የተወሰደበት ስራ ተሰርቷል። **ለምሳሌ** የኮቪድ 19 ወረርሽን በመከላከል የተሻለ ስራ ተሰርቷል። ሌሎች በመከላከል ረገድ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ያለው ስራ የሚበረታታ ነው። ነገር ግን አሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ኮቪድ 19 መልኩን እየቀየረ መምጣት፣ በጦርነቱ ምክንያት እየተፈናቀለ ያለው ዜጋ መብዛት የማህበራዊ ግንኙነታችን አጠቃላይ የተጠናከረ ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ ሁኔታ ያለ በመሆኑ ይህ ከጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና እስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አንፃር ምን አንደምታ እንዳለው አስቦ መስራት ተገቢነት ይኖረዋል። አሸባሪዉ ባደረሰዉ ወረራ ምክንያት የወደሙ የጤና

ተቋማት፣ቅርሶቻችንና የእምነት ተቋማት መኖራቸው በዚህ ምክንያት የማንደርስላቸው ዜጎች መኖራቸው፣ የህጻናት፣ የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች አጠቃላይ ማግኘት የሚገባቸውን ያለማግኘት፣ እስካሁን ያለው ብቻ ሳይሆን እንደገና መገንባት እና ዜጎችን የማገልገል ተግባር ቋሚ ኮሚቴው በሚገባ የሚገነዘበውና የሚከታተለው ይሆናል። በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አዎንታዊ የሆነ የማህበራዊ መስተጋብራቸዉ ተዛብቶ በስነ ልቦና ቀዉስ ላይ እንደሚገኙ ብዙ ጠቋሚ ሁኔቶች እንዳሉ ያመላክታሉ። በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ቀዉስ ከማስከተሉም በተጨማሪ ያስከተለዉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶችን ተገንዝቦ ቋሚ ኮሚቴዉ ሀላፊነቱን መወጣት ይገባዋል።

## 1.4. የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሁኔታ

በሀገራችን 6ኛ ዙር ምርጫ ሲካሄድ ህዝቡ ይሆነኛል ያለውን በነፃነትና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መርጧል። በዚህም ከም/ቤቱ አባላት ውስጥ በጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ የባህልና ስፖርት ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ 13 አባላት ተደልድሏል። በ3 ንኡስ ኮሚቴ በመከፋፈል ለስራው ውጤታማነት ያመች ዘንድ ተደራጅቷል። የዚህ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ከተለያዩ የሙያ ዲሲፕሊን፣ የተለያዩ የስራ ልምዶች እና የፆታ ስብጥር ያላቸው በመሆኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት እንደምቹ ሁኔታ የሚወሰድ ነው። የቋሚ ኮሚቴ አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ከመውሰዳቸው በተጨማሪ ከአሁን በፊት የቋሚ ኮሚቴ ስብሳቢ በነበሩት እና በባለሙያዎቹ የስራ መጀመሪያ እና ተሞክሮ ልውውጥ መደረጉ ተነቃቅተውና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ተግባር ለመወጣት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ፣ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በብቃትና በውጤታማነት ለመስራት አቅም ይፈጥራል። ሌላው ምቹ ሁኔታ የነበረው ቋሚ ኮሚቴ የሠራቸውን አፈፃፀሞች አጥንተውና ገምግመው ለተሞክሮ ተዘጋጅቶ መቀመጣቸው ለስራው ቀናነት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ።

## 1.5. የመረጠን ህዝብ ከቋሚ ኮሚቴው የሚጠብቃቸው ጉዳዮች እንደመነሻ ተወሰዷል

የመረጠን ህዝብ ለሰላም፣ለፍቅር፣ለልማት፣ለወንድማማችነት ለመተባባበር፣ለመተዛዘንና ለመደጋገፍ የሚያስችል በጎ የዴሞክራሲ ባህሎች ያለው ህዝብ ነው ። ሀገሩን የሚወድ

ሉአላዊነቱን አሳልፎ የማይሰጥ በመሆኑ ከዚህ ህዝብ መፈጠር ፤ በዚህ ህዝብ መመረጥና ለዚህ ህዝብ ማገልገል መታደል እና እንደጥሩ አጋጣሚ በመቁጠር የህዝቡን በሀቀኝነትና በታማኝነት ማገልገል ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ከቋሚ ኮሚቴው የሚጠበቀው ተጠያቂነት ያለው የክትትልና ቁጥጥር ስራ መስራት፤ ፍታዊነት እንዲኖር፤ የህዝብ ጥያቄዎች እንዲደመጥና እንዲፈታለት ለማድረግ ጥረት ማድረግ አጠቃላይ ከይስሙላ የወጣ አሰራር በመዘርጋት የመንግስትን አቅም ያገናዘበ ልማት እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡ በየሄዱበት ቃል መግባት ህዝብን መዋሸትና ማታለል በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው በመገንዘብ የህዝብ ውክልናን መወጣት ተገቢ ነው፡፡

### 1.6. የምክር ቤቱ የ5 አመት ስትራቴጂክ እቅድ እንደመነሻ ተወስዷል

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 6ኛውን ብሔራዊ ምርጫ ተከትሎ የተመሰረተ አዲስ ም/ቤት እንደመሆኑ መጠን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ውስጥም ሆኖ በአገራችን የተጀመረውን የለውጥ ንቅናቄ ለማስቀጠል የሚያግዙ ፖለቲካዊ፣ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስርዐትን አስመልክቶ ያለውን ሀገራዊ ሁኔታ የዳሰሰና የቃኘ ሲሆን ውጤታማ የህዝብ ውክልና ሥራን ለማከናወን የሚያስችል አሰራርና አደረጃጀት በማጠናከር የምክር ቤቱን የስራ ሁኔታ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ጥራትና አግባብነት ያላቸው ህጎችን ከማውጣት፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ሲሰሩ ዕውቀትንና መረጃን መሠረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ አሰራርንና መፍትሄ ሰጭነትን ያረጋገጠ እንዲሆን፤ የአስፈፃሚውን አካል ተጠያቂነት ከማረጋገጥ፤ ዕውቀትና መረጃን መሰረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ የምክክርና ክርክርን ባህል ከማሳደግ በቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ የልማት፣ የዴሞክራሲ ግንባታ፣ የሰላምና የፀጥታ ማስፈን ውስጥ ጉልህ ሚና በመጫወት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ማለትም የሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና በጤናው ዘርፍ የስነ ተዋልዶና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተኮር ሥራዎችን ከማጠናከር አኳያ አቅዶ የተነሳ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴውም ይህንን እንደ መነሻ በመውሰድ የራሱን እቅድ ለአተገባበር በሚያመች መልኩ አዘጋጅቷል፡፡

### 1.7. የምክር ቤቱ የ2014 እቅድ እንደመነሻ ተወስዷል

ከምክር ቤቱ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በመነሳት የ2014 በጀት አመት እቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በመግባት ላይ ያለ ሲሆን ከዝግጅት እስከ ማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራትን በተለያዩ ውጤት ተኮር ግቦችና ዝርዝር ተግባራት ሸንሽኖ አዘጋጅቷል፡፡ እቅዱ በዋና ዋና ግቦች ማለትም

የአቅም ግንባታ ስራዎች፤ ሕግ የማውጣት፤የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ፤የሕዝብ ውክልና ተግባራት፤ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ስራዎች፤የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች እና ዋና ዋና ተግባራት፤ የም/ቤቱ ጽ/ቤት ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች እና ዋና ዋና ተግባራት በማለት በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴውም ይህንን መነሻ በማድረግ ጉዳዮች የራሱን እቅድ አዘጋጅቷል፡፡

## 1.8. የ2013 በጀት አመት የቋሚ ኮሚቴው እቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ ተወስዷል

### 1.8.1. የአቅም ግንባታ ስራዎች እንደ መነሻ ተወስደዋል

ቋሚ ኮሚቴው አላማውንና ተልእኮውን ለማሳካት የሚያስችለውን አቅም በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥ፣ በትምህርታዊ ጉብኝቶችና በተለያዩ የውይይት መድረኮች ለስራው አጋዥ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን እንዲሁም በምክር ቤቱ በሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በመሳተፍ አቅማቸው እንዲጐለብት ተደርጓል፡፡ የተሰጡ ስልጠናዎችን ከምንከታተላቸው መስሪያ ቤቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ብቃት ያለው የክትትል፣ቁጥጥር እና ድጋፍ ለማድረግ የሚያዘጋጅ አቅም እንዲፈጠርላቸው ያደረገ እና ስራዎቻቸውን በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን አስችሏል፡፡ የውስጥ አቅምን ለማጎልበት በተቋቋመው የአቅም ግንባታ ኮሚቴ አማካኝነት ይመራ የነበረው የርስ በርስ መማማሪያ መድረኮች በተወሰነ ደረጃ ውስንነት የነበራቸው ሲሆን በዚህ አመትም ይህን ተግባር በማሻሻል ተጠናክሮ አጠናክረን የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 1.8.2. የህግ አወጣጥ ተግባራችን እንደ እቅድ መነሻ ተወስዷል

- በበጀት አመቱ ውስጥ ለቋሚ ኮሚቴዎች በርከት ያሉ የተለያዩ አዋጆች በዋናነትና በተባባሪነት የተመሩለት አዋጆች በብቃት ህዝብን ያሳተፈ ስራ በመስራት የበሰለ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ የተሻለ ስራ ተሰርቷል፡፡
    - የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችን እቅድ ግምገማና ግብረ መልስ የሪፖርት ምርመራና ግብረ መልስ እንዲሁም መደበኛና ድንገተኛ የመስክ ምልከታዎች በሚደረጉበት ጊዜ የወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መፈፀማቸው እየተረጋገጠ እንዲሄድ በተያዘው አቅጣጫ መሰረት የክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን ለመፈፀም ተችሏል፡፡

- በዓመቱ ለጋራ ምርመራ ከተመሩ ረቂቅ ህጐች በዋናነት ከተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ውጪ በተባባሪነት ረቂቅ ህግ እንዲመረምሩ የሚመራላቸው ኮሚቴዎች ያላቸው የምርመራ ተሳትፎ ውስን ነበር፤ይህም ለአሁኑ ቋሚ ኮሚቴ ትምህርት ይሆናል፡፡

### 1.8.3. የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት እንደመነሻ ተወስዷል

- የህዝብ ዘላቂ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የተያዙ ግቦች ከስትራቴጅክ እቅድ መነሳቱን እና በታቀደው መሰረት አፈጻጸሙን በመገምገም የመስክ ምልከታ እና የውክልና ስራዎች ሪፖርቶች ለማየት ተችላል፡፡
- ቋሚ ኮሚቴው ተግባራትን ከሪፖርት ባለፈ የአካል ምልከታ በማድረግ ያለበትን ሁኔታ ለመገምገም በዓመት 4 የመስክ ምልከታዎችን ለማከናወን አቅዶ ባቀደው መሰረት ሁሉም ተከናውኗል፡፡መስክ ምልከታው ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ወደ ተመረጡ ክልሎች በመሄድ ሲሆን የመስክ ምልከታዎች በጤና፣ በባህልና ቅርስ እንዲሁም በስፖርት፣በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ እና በሴቶች፣ህፃናቶችና በወጣቶች ዘርፍ ሲሆን የመስክ ቡድኑ በየደረጃው ለሚመለከተው አካል ከተቋማት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ግብረ መልሱን ሰጥቷል፡፡

### 1.8.4. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እንደ መነሻ ተወስዷል

መንግስት ለመልካም አስተዳደር ስራዎች ትኩረት መሰጠት እንዳለበት እና ኮሚቴው በእቅድ፣ በክትትል እና ቁጥጥር ስራዎችም ሆነ በመስክ ምልከታ በልዩ ሁኔታ በትኩረት መስራት እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም በአመቱ ስራው ከእቅድ ምርመራ ጀምሮ የተሰራው ስራ ግን አጥጋቢ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በተለይም ክትትል በሚደረግባቸው አንዳንድ ሴክተሮች ከእቅድ ጀምሮ ያለመላክ እና ሪፖርቶቻቸው ላይ የተከናወኑ የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ትኩረት አድረጎ ያለማከናወን ተስተውለዋል፡፡ በሌላ በኩል በኮሚቴው ውስጥ የመልካም አስተዳደር ስራን በማስፈን ረገድ የሀገር ውስጥና የውጪ ስልጠናዎችን፤ የመስክ ስራዎች እና በሌላ አካላት በሚዘጋጁ የተለያዩ ወርክሾፖችና ሴሚናር ላይ አሳታፊ እንዲሁም ፍትሀዊ በሆነ

መልኩ የተከናወኑበት አግባብ የተሻለ ስለነበር  በዚህ አመትም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

### 1.8.5. የባለብዙ ዘርፍ ተግባራት እንደ መነሻ ተወስዷል

- ቋሚ ኮሚቴው ይህ ዘርፍ በዋናነት የሚመለከተው በመሆኑ የዓለም የኤድስ ቀን፣የአድዋ በዓል፤የስፖርት ፌስቲቫሎች፤የፀረ ፆታ ጥቃት (ነጭ ሪባን) ቀን፣የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8) እንዲሁም በመስክ ምልከታዎችናበየሪፖርት ግመገማ ወቅት ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በሚመለከት የስርዓተ ጾታ ጉዳይ፤ የአካል ጉዳተኛና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተግባራት፣ ስለ ህፃናት ማቆያና ስለ አከባቢ ጥበቃ የትኩረት ነጥቦች መሆናቸውን  በቼክ ሊስት በማካተት የመከታተል ስራ በመሰራቱ ለቋሚ ኮሚቴው ስራ ጥሩ መነሻ ይሆናል፡፡
- ምክር ቤቱ ለሚያሳድጋቸው 29 ታዳጊ ህፃናት በየወሩና በበዓላት ጊዜ  ከምክር ቤቱ ጽ/ቤት የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በእናት አባሳደሮች ጋር እየተሰራ ስለነበር ይህ ተግባር እንዳይቋረጥ መስራት ይጠይቃል፡፡

### 1.9 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የ2013 በጀት አመት አፈጻጸም እንደ መነሻ ተወስዷል

- ቋሚ ኮሚቴው ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የሚችለው ተገቢውን አስተዳደራዊ ድጋፍ፤ሎጀስቲክስ (የትራንስፖርት፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፤የሚዲያ ሽፋን፤ የመስተንግዶ) እና ሙያዊ ድጋፍ ከጽ/ቤቱ ሲያገኝ ነው፡፡ የምክር ቤቱ ድጋፍ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ እየተጠናከረ መምጣቱ ይህም የበለጠ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የምክር ቤቱ ጽ/ቤትም እቅዳችንን አቅም በፈቀደ መጠን የመደገፍ ሚና እንደሚወጣ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

### 1.10  የቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች፣

**በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች፡-**

- በአመራሩም ሆነ በአባላት የስራ ተነሳሽነት መኖሩ፤
- አባላት የተሰጣቸውን ተልዕኮና ተግባር በትጋት፣ በውጤታማነትና በቅልጥፍና መከናወናቸው፣
- በአብይና በንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በስፋት መሳተፍና ሃሳቦችን ማንሸራሸር መቻላቸው።
- አባላት የተያዘዉን ዕቅድ ለማሳካት ተጨማሪ ጊዜ ወስደዉ የሚሰሩበት ሁኔታ መኖሩ፤
- በተጣበበ ጊዜ ዉስጥም ሆነው ለመስክ ምልከታ የተመደቡ አባላት ጥሩ ስራ መስራት መቻላቸዉ፤
- ሴክተሩን የሚከታተሉ አባላትን በአካል ለየብቻቸው በመጥራት ሪፖርቱን የጋራ በማድረግ ለተቋማት በወቅቱ እንዲደርስ መደረጉ፤
- በአመራሩ በኩል በወቅታዊ የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ የተፈጠሩ ችግሮችን በመቋቋም ሴክተሩን ከሚከታተሉ አባላት ጋር በጋራ በመገምገም የሪፖርት ግብረ መልሶችን ለተቋማት እንዲላክ መደረጉ በጥንካሬ የተጠቀሱ ተግባራት ናቸው።

**በእጥረት የታዩ ጉዳዮች፡-**

- የአባላት በተለያዩ ምክንያቶች ከስራ መጓደልና መንጠባጠብ መኖሩ፤
- የአቅም ግንባታ ኮሚቴው በተለያዩ ምክንያቶች የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ በጊዜ መጣበብና የስራ መቆራረጥ በመኖሩ በታቀደው ልክ ስራውን አለማከናወኑ፣
- በሌላ በኩል ምንም እንኳን የቋሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባዎች በተገቢ መንገድ የተጠቀምንበት ቢሆንም የንኡስ ኮሚቴዎች የስራ ቀንን መጋፋት እና በሌሎች ስብሰባዎች ምክንያት ወቅቱን ጠብቆ ያለመሰብሰብ ችግሮች ነበሩ።

## 1.11 የአስፈፃሚ አካላት የ2013 በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች

**በጥንካሬ የሚታዩ ጉዳዮች**

- የበጀት አመቱን እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ አመቱ መላካቸው፤
- ከሚከታተላቸው ቋሚ ኮሚቴ ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ መሆኑ፤

- የተወሰኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ዕቅድ በሚዘጋጅበት ሂደት ውስጥ የነበሩ ክፍተቶችንና ችግሮችን በማስወገድ የተከለሰውን ዕቅድ መላኩ፤
- የታቀዱ እቅዶች ከስትራቴጂክ ግቦች፣ ከGTP,ከ SGD ከአፍሪካ መንግስታት እቅድ ጋር የተጣጣመ መሆኑ፤

**በእጥረት የታዩ ጉዳዮች፡-**

- ተቋማት በቋሚ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን ግብረ መልሶች ተቀብለው መተግበርና የወሰዷቸውን ማስተካከያዎች ማሳወቅ ላይ ውስንነቶች መኖራቸው፣
- በዕቅዱ ውስጥ የተቋሙን ቁልፍ ችግር በመለየት አለመታቀድ
- እቅዱን ከሰራተኞች፣ ከህዝብ ክንፍና ከቦርድ ጋር በአግባቡ ተወያይቶና ተግባብቶ ከመምጣት አንፃር ክፍተቶች መኖራቸው፤

## 1.12 በቋሚ ኮሚቴው የሚገኙ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች በ2013 ዓ.ም በጀት ዓመት የአፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች እንደ መነሻ ተወስዷል

በቋሚ ኮሚቴው ወደ 13 የሚጠጉ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ያሉ ሲሆን ባለሙያዎቹ የተለያዩ አስተዳደራዊና ሙያዊ ድጋፎችን እየሰጡ የቆዩ ሲሆን በዚህ ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎች ሲታዩ የተሰጣቸውን ስራ በሃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ ለመተግበር ያላቸው ተነሳሽነት ቀደም ሲል ከነበረው የተሻለ ድጋፍና አገልግሎት ለመስጠት እራስን ከማብቃትና በእውቀት ከማሻሻል አንፃር ያላቸው ፍላጎት አሁን የመጣውን ኮሚቴ በእውቀት እና በብቃት ላይ የተመሰረተ እገዛ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተያያዘ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የጥናት እንዲሁም ርፖርት መሰል ፅሁፎችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የማድረስ ስራዎች መሰራታቸው፤በም/ቤቱ ጽ/ቤቱ በኩል እንዲጠኑ በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ባለሙያዎች ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ በማጥናት ለምክር ቤቱ ብሎም ለሌሎች በግብአትነት የሚውል የጥናት ግኝቶችን ማበርከታቸው ለኮሚቴው አቅም ይሆናል።

**በእጥረት የሚጠቀሱ ጉዳዮች**

በቋሚ ኮሚቴው ያለውን አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ስርአት ክፍተት ያለ መሆኑ፤ባለሙያው ያለውን እውቀትና መረጃ ለሌሎች የስራ ባልደረባዎቹ የማካፈል ልማድ የሌለና ይህንንም ለማድረግ የተነሳሽነት ስሜቱ ያነሰ መሆኑ ታይቷል። በመሆኑም ይህ ቋሚ ኮሚቴ በድጋፍ ሰጪ ባለሙያው ያሉትን ጥንካሬዎችና የአፈፃፀም ድክመቶች በመለየት በቀጣይ በሚኖረው

የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ ሚዛን የሚደፉ ተግባራትን ለመፈፀምና የነበሩ ውስንነቶችን በማሻሻል የተሻለ አስተዳደራዊና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት የሚችልና የመፈፀም አቅሙ ሙሉ በሙሉ የተገነባ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ እንዲኖር በጋራ ከባለሙያው ጋር በቅርበት የሚሰራ ይሆናል፡፡

**መልካም አጋጣሚዎች**

- በመንግሥት ደረጃ አዲሱ የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ አገራዊ ስትራቴጅያዊ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር የተገባበት በመሆኑ በአዲስ መነሳሳት የበጀት ዓመቱን ሥራዎች ለመፈፀም መልካም አጋጣሚ መሆኑ፤
- መንግስት የጀመረው የለውጥ ጉዞ እና የተፈጠረው አገራዊ መነቃቃት እንዲሁም ህብረተሰቡ በምክር ቤቱ ላይ ያሳደረው ተስፋ፤
- መንግስት ለምክር ቤቶች መጠናከር ቁርጠኛ አቋም መያዙ እና የምክር ቤቱ አባላት እና ቋሚ ኮሚቴዎች ለውጥ ለማምጣት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ተነሳሽነት የፈጠሩበትና አዲስ ምክር ቤት እንደ መፈጠሩ አዲስ ቋሚ ኮሚቴዎችንም በማደራጀት የተሻለ ስራ የሚሰራበት ወቅት መሆኑ፤
- መንግስት የአሰራር እና የአደረጃጀት ማነቆዎች ለመፍታትና ለማስተካከል አቅጣጫ ተቀምጦ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተገባበት መሆኑ፣
- በኮሚቴው ውስጥ የተመደቡ አባላት የስራ ልምድ ስብጥሩ እና የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው አባላት መኖራቸው፣
- ምክር ቤቱ ወደ ህዝብ ተደራሽ ለመሆን እያከናወናቸው ያሉ መልካም ስራዎች ለስራው መቀለጣፍ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ይሆናል፣
- አብዛኛዎቹ አስፈጻሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ቋሚ ኮሚቴዎች የሚያደርጉትን የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በእውቀት ላይ የተመሰረተ ሚዛናዊ የሆነ እና ተጨማሪ አቅም እየፈጠረልን ነው የሚል ቀና አመለካከት እያዳበሩ መምጣታቸው፣

**ስጋቶች**

- ቋሚ ኮሚቴዎች በአገራችን በተለያዩ ክፍሎች በአሸባሪዎች በተከሰተው ጦርነት በሚታዩ ችግሮች በእቅዱ በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት የመደበኛና የድንገተኛ የመስክ ምልከታ

ለማድረግ ያለመቻል ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፣የሕዝብ ውክልና ሥራዎችንም በተሟላ ሁኔታ ለመፈጸም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፣

- በአለምና በሀገራችን የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ አሁንም በሚታየው ሁኔታ እየጨመረ ከሄደ ቋሚ ኮሚቴው በተቀመጠው እቅድ መሠረት የክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ ስራዎችን ለማከናወን ስለሚቸገርና  የእቅዶች ያለመፈፀም ስጋት ሊኖር ይችላል፡፡
- እንደ ሀገር በተለያዩ ቦታዎች የሚከሰቱ የጸጥታ ችግሮች (የሰው ህይወት መጥፋት፣ ንብረት መውደም እና መፈናቀል) በአጠቃላይ `ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ያሳቸው አሉታዊ ተጽዕኖ በስራው ላይ ማሳደራቸው ስጋት ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡

### 1.13 የመነሻ ሁኔታ ማጠቃለያ

መነሻ ሁኔታው አሁን አዲስ ለተቋቋመው ቋሚ ኮሚቴ ያለው ፋይዳ ትልቅ ነው፡፡ እስካሁን ያሉ ጥንካሬዎች እንደመልካም ተሞክሮ በመውሰድ አቅም የሚፈጠርበትና ለውጤት እንዲበቃ የሚያግዙ በመሆናቸው ይህን እንደ ግብዓት በመጠቀም ከዚህ የተሻለ ስራ በመስራት የህዝባችንን አደራ እንድንወጣ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል እስካሁን መሰራት የነበረባቸው ያልተሰሩ ስራዎች ችግር ሆነው የቆዩ በድክመት የታዩ በሙሉ በጥንቃቄ በማየት የሥራው አካል ተደርጎ ችግሮችን በመቅረፍ ውጤታማ መሆን ይገባል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው የባለቤትነት መንፈስ በመያዝ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ስራ ለመስራት የራሱን ክህሎትና ፈጠራ በመጨመር ቋሚ ኮሚቴውን ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስ እንዳለበት ያመላክታል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የ2014 በጀት አመት እቅድ

### 2.1. <u>ቁልፍ ችግር</u>

የማስፈፀም አቅም እጥረትና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ውስንነት፤

### 2.2. ቁልፍ ተግባር

የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎችን በማጠናቀቅ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በማከናወን የህዝቦችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

### 2.3. የእቅዱ ዋና ዓላማ

በሀገራችን የተጀመረውን የለውጥ ንቅናቄ ለማስቀጠል የሚያግዙ የአሰራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን በማድረግ ሁለንተናዊና ተቋማዊ የአሰራር ብቃት በማጉልበት ሥራዎችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በመታገዝ የክትትልና የቁጥጥር ስርአትን በማጠናከር ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

### ዝርዝር አላማዎች

- የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ በማስቀጠል እና መሰረታዊ አቅጣጫዎችን በመከተል ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓትን በማስፈን የተጠያቂነት አሰራርን ማስፈን፤
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸውን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ከእቅድ ዝግጅት እስከ አፈጻጸም ያለውን ውጤት በጠንካራ የክትትልና ቁጥጥር ስራ የሕዝቡን ማህበራዊ፤የወጣቶች እና የሴቶች ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እንዲሁም ጤና ነክ ችግሮች ተቃለው የባህል ስፖርት ዘርፉ እንዲጎለብትና ዘላቂ ልማት እንዲመጣ የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር፤

- የቋሚ ኮሚቴ አባላት አቅም በማጠናከር በህግ ማውጣት ሂደት ረቂቅ አዋጆች ሲመሩለት በጥራት ለማከናወን እንዲሁም የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት በውጤታማነት እንዲፈፀሙ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣
- የኮቪድ-19 ስርጭትን በመከላከል በሀገራችን ላይ የሚከሰተውን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጽእኖ እንዲቀነስ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የህግ ማስከበር ዘመቻው በሚካሄድበት ክልሎች የተፈናቀሉ ህጻናት፣ሴቶች፣ አረጋዊያን የጤና፣የምግብ፣ የመጠለያ...ወዘተ ያሉበትን ሁኔታ መከታተልና ችግራቸው እንዲቀረፍ ማድረግ፤
- ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶች በሚገባ ተጠብቀውና እየለሙ መሆናቸውን የመከታተልና በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ የመገንባት ስራዎችን በትኩረት መከታተል፣
- የአገራችን ልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ እንዲለሙ፣ ስነ-ጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ መፈጠራቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

## 2.4. የእቅዱ ግቦችና ዓላማ

ቋሚ ኮሚቴው ግቦችን በመቅረጽ ጠንካራ የክትትል ቁጥጥር ስራ በመስራት ዘላቂ ጤና ነክና የማህበራዊ ልማት እንዲጐለብት፤ የወጣቶች እና የሴቶች ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት እንዲያድግ የባህልና ስፖርት ስራዎች ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ የተሰጠውን ህዝባዊ ኃላፊነትና ተግባርን በብቃት እንዲወጣ ማድረግ ነው::

### 2.4.1. የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች

**ግብ 1**፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላትን አቅም ማሳደግ፣

**ግብ 2**፡ ረቂቅ ህጐችን በመመርመር እንዲፀድቁ ማድረግ ፣

**ግብ 3**፡ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን ማከናወን፣

**ግብ 4**፡ የሕዝብ ውክልና ተግባርን መወጣት

**ግብ 5**፡ ቅሬታና ጥቆማን በመመርመር ምላሽ መስጠት

**ግብ 6**፡ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን መከታተልና ማስፈፀም

**ግብ 7**፣ መረጃ ማሰባሰብና ማደረጃት

**ግብ 8**፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ (የዴሞክራሲ ባህልን ማጎልበት)

### 2.4.2. የ2014 እቅድ ዝርዝር አፈጻጸም

የ2014 በጀት አመት እቅድ ለትግበራ አፈፃፀም ምቹ እንዲሆን በሦስት ምዕራፍ ተከፋፍሏል፡፡

**እነዚህም፡-**

I. የዝግጅት ምዕራፍ (እስከ ህዳር 2014 ዓ.ም)
II. የተግባር ምዕራፍ (ከህዳር እስከ ግንቦት 2014 ዓ.ም)
III. የማጠቃለያ ምዕራፍ (ሰኔ 2014 ዓ.ም)

### 2.5. በዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የኮሚቴውን የ2014 ዓ.ም እቅድ በምክር ቤቱ መሪ እቅድ ጋር እንዲጣጣም መከለስ እና የስራ መከታተያ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ከአባላት ጋር ገምግሞ የጋራ በማድረግ ለሚመለከታቸው አመራሮችና የስራ ክፍሎች ይልካል፤
- ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው አስፈፃሚ ተቋማት ጋር የትውውቅና የቀጣይ አቅጣጫ ስራዎች ላይ የጋራ መግባቢያ መድረክ ይዘጋጃል፤መስሪያ ቤቶችን ቀድሞ ይጎበኛል ከጉብኝት ማግስት መኒስትሮች ያዘጋጁትን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- ንዑሳን ኮሚቴዎችም የአብይ ኮሚቴውን እቅድ መነሻ በማድረግ የራሳቸውን እቅድ እና የመከታታያ ቼክ ሊስት ያዘጋጃሉ፣
- ሁሉንም የምንከታተላቸውን አስፈፃሚ መስሪያ የተመረጡ ተጠሪ ተቃማትን የቅድሚያ ጉብኝት ማድረግ
- ከጉብኝት በሃላ እቅዳቸውን እንዲያስተዋውቁ መጥራት
- ሁሉንም የምንከታተላቸውን አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የ2014 ዓ.ም እቅዳቸውን እና የ1ኛ ሩብ አመት ሪፖርት መገምገም እና ግብረ መልስ መስጠት፤
  - እቅዱ ችግሮችን በትክክል የዳሰሰና ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፤ በአለፈ አመት ያልተከናወኑ ተግባራት በዚህ አመት ለማከናወን በእቅድ ውስጥ ስለመካታተቻው ክትትል ማድረግ፤
  - እቅዱ ከሴክተሩ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፤ ስትራቴጂዎች እንዲሁም ከ5 እና ከ10 ዓመት መሪ እቅድ ጋር የተጣጣመ እና የተናበበ መሆኑን ማረጋገጥ፣

- ከሰራተኛው ጋር ውይይት ስለመደረጉ እና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት መስጠት፣
- የተቋማቱን አጠቃላይ የ1 ኛ ሩብ አመት አፈፃፀም ምን እንደሚመስል በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት፤
- ለሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የኤች አይቪ ኤድስ፤የአካል ጉዳተኞች ኮንቬክሽን አተገባበር፣እና የወጣቶች እና የሴቶች ጉዳይ ለእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴዎች ለሚከታተሏቸው ሴክተሮች ክትትል እንዲያደርጉ ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ መላክ፣
- ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የሚላኩ ሴክተር ዘለል ቼክ ሊስቶች ካሉ የስራዉ አካል አድርገዉ መስራት በተለይ እቅድ ላይ በትኩረት መስራት፣

- የጤና፣ ማህበራዊ ልማት እና ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና የምክር ቤቱ ጽ/ቤት የኤድስ ግብረ ሀይል በጋራ የሚሰራውን ስራ አጠናክሮ ለመቀጠል የማስፈጸሚያ እቅድ በእናት አምባሳደሮች እና በግብረ ኃይሉ እንዲዘጋጅ መደገፍ፣
- የኤድስ ፈንድ አጠቃቀም እና የህጻናት ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማስተባበር የቅድመ ዝግጅት ሥራን ማስጀመር፣
- ቋሚ ኮሚቴው ስለሚከታተላቸው አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች አባላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የቅድመ ዝግጅት ስራን መገምገምና የቀጣይ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፤

## 2.6. የተግባር ምእራፍ (ከህዳር -ግንቦት)

### 2.6.1. አቅም ግንባታ

**ግብ 1** የቋሚ ኮሚቴ አባላትን አቅም ማሳደግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፤** በእውቀት ላይ በተመሠረተ ብቃት የተከናወኑ ተግባራት

#### ዋና ዋና ተግባራት፡-

- ቋሚ ኮሚቴው ለሥራዉም ሆነ ለፓርላማው አዲስ በመሆኑ ስራውን በእውቀት እና በበቂ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ስለመስሪያ ቤቶቹ ስልጣንና ተግባራት እቅዳቸውን እና የአሰራር ስርአቱን ማወቅ ስላለበት የአቅም ግንባታ መድረኮች መዘጋጀት አለባቸው፡፡ የአቅም ግንባታ ኮሚቴ በሚያዘጋጃቸው በፖሊሲዎች እና

ስትራቴጂዎች እና አሰራሮች ወዘተ ዙሪያ በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ የመማማሪያ እና የአቅም መገንቢያ ኮሚቴ ማዋቀር እና የስልጠና ርእሶችን በመለየት የውስጥ አቅምን ማጎልበት፤

- በምክር ቤቱ በሚቀርቡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሌሎች ተዛማጅ የአቅም ግንባታ መድረኮች የቋሚ ኮሚቴ አባላት በብቃትና በንቃት መሳተፍ ይጠበቃል፣
- በምንከታተላቸው መ/ቤቶች የሚሰጡ ለክትትልና ቁጥጥር ሥራ አጋዥነት ባላቸው ስልጠናዎችና ወርክ ሾፖች ላይ እንዲሁም የውስጥና የውጪ ጉዞ ምልመላ ላይ አባላት ፍትሀዊና አሳታፊ በሆነ መልኩ አቅማቸውን እንዲገነባ ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፣ ይህም የሚመለከተው አካል ሲፈቅድ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
- በምክር ቤቱ፤ በፅ/ቤቱ፤ በቋሚ ኮሚቴ እና በተጠሪ ተቋማት በሚዘጋጁ አቅም ግንባታ ስልጠናዎች አባላትና ባለሙያዎች የሚሳተፉ ይሆናል፡፡
- ከምንከታተላቸው መ/ቤቶች ውጭ ማለትም በሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የሚመጡ ስልጠናዎች ጠቃሚነታቸውን በኮሚቴ ደረጃ እየመዘኑ መሳተፍና የስልጠናውን ውጤት ለቋሚ ኮሚቴው በሪፖርት ማሳወቅ፣ ሪፖርቱ ለኮሚቴው ሥራ ግብዓት ሆኖ እንዲያገለግል አድርጎ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
- የምንገነባው አቅም ሁለንተናዊ የዴሞክራሲ ባህልን ያጎለበተ ማለትም ግልጸኝነት ፤አሳታፊነት በጋራና በትብብር መስራት ፤ቡድኑን አጠናክሮ ይዞ መውጣት ፤በቶክኖሎጂ መታገዝና ዘመናዊ አሰራር መፍጠር ፤ ውጤታማነት ያረጋገጠ መሆን ይገባዋል፡፡

## 2.6.2. የህግ ማውጣት ግብና ዋና ዋና ተግባራት

**ግብ.2** ረቂቅ ህጐችን በመመርመር እንዲፀድቁ ማድረግ

**የሚጠበቅ ውጤት** 1. በጥልቀት ተመርምረው የፀደቁ ጥራት ያላቸው ህጐች ፤

### <u>ዋና ዋና ተግባራት</u>

- ከምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው ለዝርዝር እይታ የተመሩ ረቂቅ አዋጆችና ስምምነቶችን በጥልቀት መመርመር፤
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት /አስረጂዎች/ ጋር በረቂቅ ህጉ ዙሪያ ለመወያየት መድረክ ማዘጋጀት፣

- በረቂቅ ህጉ ዙሪያ የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ሀሳብ ማሰባሰብ፣
- ለባለድርሻ አካላት ረቂቅ ህጉን አስቀድሞ በመላክ በህዝብ ይፋ ወይይት መድረኮች ባለድርሻ አካላትና ግለሰቦችን ጭምር በአካል ተገኝተው እንዲሳተፉ ባይችሉ ደግሞ በረቂቅ ህጉ ላይ ያላቸውን አስተያየት በጽሁፍ በተለያዩ ዘዴዎች ለቋሚ ኮሚቴ እንዲልኩ በመጋበዝ ሀሳብ ማሰባሰብ፣
- ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በጋራ የሚመሩ ረቂቅ አዋጆች ካሉ በንቃት መሳተፍ፤
- ረቂቅ አዋጁ ዜጎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን መብቶችና ግዴታዎች ህጋዊ ከለላ እንዲያገኙና በአስፈጻሚ አካላት ዘንድ የአገልጋይነት፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር የሚያሰፍን መሆኑን መርምሮ ማረጋገጥ፣ ህጉ ለህብረተሰቡ ካለው ጠቀሜታ አንጻር ታይቶ ጥራቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲፀድቅ የመለየትና የውሳኔ ሃሳብና አስተያየት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፀደቅ፣
- ለምክር ቤት የሚቀርቡ ረቂቅ አዋጆች ክህገ-መንግስቱ፣ ከፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንዲሁም ከመንግስት የ10 ዓመት መሪ እቅድ ጋር መጣጣማቸው፣ በቂ ጥናት የተደረገባቸው መሆኑ እንዲሁም የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

## 2.6.3. የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ግብና ዋና ዋና ተግባራት

**ግብ.3** የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን ማከናወን፣

የሚጠበቅ ውጤት፡- 1. የተረጋገጠ ተጠያቂነት፣ የተቀናጀ፣ በበቂ ዝግጅት እና በእውቀት ላይ የተመሠረተ የክትትልና ቁጥጥር አግባብ፤

2. ለታለመለት ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የመንግስት ሀብትና ንብረት፤
3. ውጤትን ያመጣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ

### ዋና ዋና ተግባራት

- እቅዱ አገራዊ መሪ እቅድን መሠረት አድርገው መዘጋጀታቸው እንዲሁም ተቋማት ከተሰጣቸው ስልጣንና ተልዕኳቸው አንፃር መሰረት ባደረገ መልኩ የታቀዱና የተፈፀሙ መሆናቸውን፤በማረጋገጥ ግብረ መልስ የሚሰጥና ለግብረ መልሱ አፈፃፀም ክትትል የሚደረግ ይሆናል፡፡

- የክትትልና ቁጥጥር ዋነኛ ዓላማ የአስፈፃሚ አካላት የእቅድ አፈፃፀም አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ህግን መሠረት አድርጐ መከናወኑ እና ውጤት የተመዘገበ መሆኑን፤
- ውጤታማነትን ያረጋገጠ ተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ እና በቴክኖሎጅ የታገዘ ስራ መስራት
- የተጀመሩ ስራዎች በሚገባው ወጭ ጊዜ ለታላመለት አላማ እንዲውል ተደርጎ ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ፡፡
- ሀላፊነታቸውን በተገቢው ለፈጸሙ ማበረታታት ላበላሹ ተጠያቂ ማድረግ
- ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት ህግንና አሰራርን በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋላቸው፤
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው ተቋማት በሀገራችን የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ለመግታት በእቅዳቸው አካተው በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆናቸው በልዩ ትኩረት ክትትል የሚደረግ ይሆናል፤ በተጨማሪም በኢትዮጲያ ላይ የተቃጣው ወረራና ጦርነት ያስከተለው በጤና ተቋማት ላይ የደረሰውን ጥፋት ለማስተካከልና እንደገና ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ማየት፤
- ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መ/ቤቶች ኦዲት መደረጉን መከታተል፣ በተሰጠው አስተያየት መሰረትም ከመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር በመተባበር መፍትሔ ማፈላለግ፣ በተጨማሪም በዋና ኦዲተር እንዲሁም በመስክ ምልከታችን ይስተካከሉ የተባሉ ጉዳዩች ስለመስተካከላቸው እና በእቅድ ውስጥ ስለመካተታቸው ማረጋገጥ

### 2.6.3.1. የአስፈፃሚ አካላትን ሪፖርት መገምገም

ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች ሪፖርቶችን በየሩብ ዓመቱ በጥልቀት በመመርመር የጽሑፍ ግብረ መልስ መስጠት፤በተጨማሪም በአካል በመጥራት የሚገመግም ሲሆን የአካል እና የፁሁፍ ግብረ መልስ የሚሰጠው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፤

**ሀ. የ1ኛ ሩብ አመት አፈፃፀምን መገምገም**

የ1ኛ ሩብ ዓመት በአብዛኛው የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት ስለሆነ አስፈጻሚዎች በሚመጡበት ወቅት የዝግጅት ምእራፍ አፈጻጸማቸውን ገለጻ እንዲያደርጉ መጋበዝ እና ከዚያ በመነሳት የተላከውን የሩብ አመት አፈፃፀም በኮሚቴ ደረጃ በጋራ መገምገም፣ ግብረ መልሱንም መስጠት፣

**ለ. የ2ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት መገምገም በተመለከተ**

- የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ6 ወር እቅድ አፈጻጸማቸውን ገምግሞ የፅሁፍ ግብረ መልስ መስጠት፤
- የጤና ሚኒስቴርን ጥር ወር ላይ በአካል በመጥራት የ6 ወር ሪፖርት በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት፤
- የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን የ6 ወር አፈፃፀማቸውን በመገምገም የፅሁፍ ግብረ መልስ መስጠት፣
- ቋሚ ኮሚቴው ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ ተጠሪ ተቋማትን እንደ አስፈላጊነቱ በአካል በመጥራት የሚገመግም ሲሆን ዝርዝሩን በንዑስ ኮሚቴዎች የሚገለፅ ይሆናል፡፡

**ሐ. የ3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት መገምገምን በተመለከተ**

- በመጋቢት ወር የፌዴራል ጤና ሚኒስቴርና ተጠሪ መስሪያ ቤቶችን አፈጻጸማቸውን በመገምገም የጹህፍ ግብረ መልስ መስጠት፤
- የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መጋቢት ወር ላይ የ9 ወር እቅድ አፈጻጸማቸውን በአካል በመጥራት መገምገም እና ከግምገማው በመነሳት ግብረ መልስ መስጠት፤
- የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን የ9 ወር ሪፖርቱን ገምግሞ የጹህፍ ግብረ መልስ መስጠት፣

**መ. ለምክር ቤቱ በቀጥታ ሪፖርት የሚያቀርቡ መስሪያ ቤቶችን በተመለከተ**

ከሚንከታተላቸው አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚያቀርቡ ሴክተሮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

- ጤና ሚኒስቴር ለምክር ቤቱ መጋቢት ወር ሪፖርት ያቀርባሉ፤

- የሴቶችና ማህበራዊ ሚኒስቴር ለምክር ቤቱ ጥር ወይም ታህሳስ ወር ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
- የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ለምክር ቤቱ መጋቢት ወር ላይ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
- ለምክር ቤቱ በቀጥታ ሪፖርት የሚያቀርቡ መስሪያ ቤቶች ሪፖርታቸውን እንዲያቀርቡ ለማመቻቸት ቀደም ብሎ ዝርዝር ሪፖርቱን በፅሑፍ ተቀብሎ በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ በመገምገም መወያየት እንዲሁም በምክር ቤቱ ለመስሪያ ቤቱ በሚያቀርቡት ጥያቄዎች ዙሪያ የጋራ መግባባት መድረስ፣ የምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሜቴ መስማማቱን ማረጋገጥ፤

**በአጠቃላይ ሪፖርቶች ሲገመገሙ የምንከተላቸው አቅጣጫዎች**

- ተቋማት የተሰጣቸውን ተልዕኮ መወጣታቸውን መከታተል
- ተቋማት ኮቪድ-19ኝን እየተከላከሉ መደበኛ ስራቸውን እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ሪፖርቶችን ስንገመግም ከፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች የተነሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ከሚንከታተላቸው መ/ቤቶች ጠንካራ አፈፃፀሞች እንዲሰፉ ድክመቶች እንዲስተካከሉ የመደጋገፍና አቅጣጫ የማሳየት ሥራዎችን መሥራትና በአግባቡ ባልሰሩ ተቋማት ላይ ተጠያቂነት የማስፈን ስራን ማረጋገጥ፤
- በክትትልናና በቁጥጥር ሂደት የተገኙ ጠንካራ ጎኖችና መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፤
- የምንከታተላቸው መ/ቤቶች አፈፃፀም ኦዲት መደረጉን መከታተል፣ በተሰጠው አስተያየት መሠረትም ከመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር በመተባበር ኦዲት ተደራጊ መ/ቤትና ከዋና ኦዲተር መ/ቤት ሀላፊዎች ጋር የዉይይት መድረክ ላይ መሳተፍ፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሌብነትና ለብክነት በር የሚከፍቱ አሠራሮች የተገኙ ካሉ በጋራ ውይይት መፍትሄ ማፈላለግ፤
- በሚንከታተላቸው መ/ቤቶች የዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚያደርጋቸውን የኦዲት ሥራና ግኝቶችን በሚመለከት የተሰጡ ምላሾችና ማስተካከያዎች በሪፖርታቸው መካተቱን መከታተል፤

- ለ2014 ዓ.ም የተያዘው በጀት አጠቃቀሙ እንዴት እንደተፈፀመ እና ምን ውጤት እንዳስገኘ ትኩረት ማድረግ፤
- ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከልና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ከመ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት አኳያ ቃኝተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተል፤
- ሪፖርቶች ሲገመገሙም ሆነ ግብረ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ የሴቶች ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት እንዲሁም የሴክተር ዘለል ተግባራት ከሴክተሩ አኳያ ምን ያህል በጥልቀት እየተሰራ እንደሆነ በትኩረት ይሰራል፡፡

### 2.6.4. የመስክ ምልከታ ተግባራት

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መ/ቤቶች በሪፖርት ካቀረቧቸው ጉዳዮች በተጨባጭ የሕብረተሰቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ መፈፀማቸውንና በተመረጡ ቦታዎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ተገኝቶ የታቀዱት ተግባራት መሬት ላይ መውረዳቸውን ማየትና ግብአት መስጠት የተሰጡ ግብረ መልሶች ወደ ተግባር መለወጣቸውን ማረጋገጥ፤

#### 2.6.4.1. መደበኛ የመስክ ምልከታ:-

**መደበኛ የመስክ ምልከታ የሚካሔድባቸው ቦታዎች፡-**

**በመጀመሪያ ዙር / ታህሳስ ወር**

- ✓ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ፊንፊኔ ዙሪያ የሚከናወኑ የከተማና የከተማ ዙሪያ፣

**በሁለተኛ ዙር /ጥር ወር**

- ✓ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
- ✓ አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

**በሦስተኛው ዙር/ መጋቢት ወር**

- ✓ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

**አራተኛው ዙር/ ሚያዚያ ወር**

- ✓ ሶማሊያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

**የመስክ ምልከታ የሚደረግባቸው ጉዳዮች ፦**

1. <u>ከጤና አኳያ</u>

- የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ተግባራት አፈጻጸም፣ የእናቶችንና ህጻናት ሞት ቅነሳ፣ የጤና ኤክስቴንሽን አተገባበር፣ የመረጃ አያያዝና አደረጃጀትን በሚመለከት፣ የጤና መድህን ትግበራ፤ የስነ ተዋልዶ ጤናና የቤተሰብ እቅድ አገልገሎት፣ የሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢዎችና ጤና ኬላዎች አገልግሎት አሰጣጥ በተለየ ትኩረት ይታያል፣ የስርአተ ምግብ/ Nutrtion/፣ የወረርሽኝ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር የተሰሩ ስራዎችን በሚመለከት፣ የመድሐኒትና የህክምና መሳሪያዎች  አቅርቦት፣ የህገወጥ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥርን በሚመለከት፣ በዩኒቨርሲቲዎችና ክሊኒኮች ተገቢ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና ለልጃገረዶች እና ለወጣቶች ተስማሚ አግልግሎት እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስጋትና በመከላከል ረገድ እየተፈፀሙ ያሉ ስራዎች ማየት፣
- በጦርነቱ የተጎዱ የጤና ተቋማት መልሶ መገንባቸውና መደራጀታቸው ክትትል ማድረግ፣

2. **ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አንጻር**

የሴቶች፤የአረጋዊያንና አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት የህጻናት እና ወጣቶች ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት፤የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ፤ የህጻናትን መብት እና ደህንነት ከመጠበቅ  በተመለከተ በመስክ ምልከታችን ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዩች ሲሆን ሌሎች እንደ አስፈላጊነታቸው የሚካተቱ  ይሆናል፡፡

3. **ከባህል እና ስፖርት አኳያ**

- ባህልና ስፖርት በሀገራችን ገጽታ ግንባታ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ከዚህም በተጨማሪ ስፖርት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር እንዲሁም  የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማእከላት መስፋፋታቸውን፤የሀገር በቀል እውቀቶች፤የቅርስ አስተዳደር ሁኔታ፤የቋንቋና የሀይማኖት እድገቶች፤የግጭት አፈታት፤ባህላዊ ስፖርቶች፣ ህዝባዊነት ማስፋትና ስፖርታዊ ጨዋነትን በማንገስ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችንና ጤናማ ዜጋን ለማፍራት እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፣፣

**የከተማ መስክ ምልከታን በሚመለከት**

ቋሚ ኮሚቴው በ2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማና በኦሮሚያ ልዩ ዞኖች የተለያዩ ምልከታዎችን እንደሁኔታው የሚያደረግ ሲሆን መስክ የሚካሄድባቸው ቦታዎች (ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ በንዑሳን ኮሚቴዎች በመረጧቸው ቦታዎች የሚካሄድ ይሆናል፡፡) ኮቪድ 19ኝን በመከላከል ረገድ ተግባራት እየተፈፀሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡

### 2.6.4.2. መደበኛ ያልሆነ (ድንገተኛ) የመስክ ምልከታ:-

- መረጃ ወይም ጥቆማ ሲደርሰን ወይም ከወቅታዊ ሁኔታው በመነሳት ድንገተኛ የመስክ ምልከታ ከተለመደው የመስክ ጉብኝት ወጣ ባለ መንገድ ማካሄድ፤
- በሚንከታተላቸው መ/ቤቶች ዙሪያ ጥቆማዎች ሲደርሱ እና ከምንከታተላቸው መስሪያ ቤቶች ውስጥ የህዝብ አቤቱታ የሚበዛባቸውን ሴክተሮች በመለየት የድንገተኛ መስክ ምልከታ የሚፈፀም ሲሆን በዚህም የተግባራቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ ለማስተካከል የሚከናወን የመስክ ምልከታ ማድረግና ግኝቶችን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ግብረመልስ መስጠት፤
- የምንከታተላቸው መ/ቤቶች እንዲንጎበኝ በተጠየቀው ስፍራ አስፈላጊነቱ በኮሚቴው ከታመነበት በቦታው በመገኘት ትምህርታዊ ጉብኝት ማድረግ እና ሊወሰዱ የሚገባቸው መልካም ተሞክሮዎችን መውሰድ፤

**የመስክ ምልከታ አቅጣጫዎች**

- ከሁሉም ንኡስ ኮሚቴ የተውጣጣ በአንድ ላይ የሚካሔድ ይሆናል፡፡
- የጉብኝት አላማዎችንና ለጉብኝት የሚሆኑ ቦታዎችን መለየት፤
- ለመስክ ምልከታ የሚሆን ቼክ ሊስት ማዘጋጀት እና ቼክ ሊስቱን በጋራ መገምገም፣
- ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በጋራ የምናካሔድው ምልከታ ከሁለቱም ኮሚቴዎች በተውጣጣ ቡድን የሚሰራ ሲሆን የራሱ ቼክ ሊስት እና ምልከታው የሚካሔድባቸውን ቦታዎች ይለያል፤

- በመስክ ምልከታችን ላይ የአካባቢውን ህብረተሰብ፤ ባለድርሻ አካላትንና ሰራተኞችን ለክትትል ስራችን አስፈላጊ ናቸው የምንላቸውን ኃይሎች እናሳትፋለን፤
- በወጣው ዕቅድ መሠረት የመስክ ምልከታው የሚካሄድበትን አካባቢ ለምንከታተለው መ/ቤት ኃላፊ በማሳወቅ በተለመደው አግባብ ማካሄድ፤
- ምልከታውን ማካሄድና የምልከታውን ሪፖርት መገመገም፤
- የታቀዱ በውጤት ለታለመለት አላማ መዋልን የተጀመሩ ስራዎች በወቅቱ ስለመጠናቃቃቸው ማረጋገጥ
- በጉብኝቱ የተገኙ ጠንካራ ጉኖችን እና ደካማ ጎኖች በመለየት ግብረ መልስ ማዘጋጀትና ለምንከታተለው መ/ቤት እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግ፤
- ከመስክ ምልከታ በኂላ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር ፊት ለፊት በአካል ተገናኝቶ በተሰጠው ግብረ መልስ ዙሪያ መወያየትና መግባባት ላይ መድረስ፤
- የመስክ ምልከታ ባካሄድንባቸው አካባቢዎች የተገኘውን መልካም ተሞክሮ በመቀመር እንዲሰፉ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግ፤
- ከምልከታ በኂላ የመጡ ለውጦችን እና የተወሰዱ እርምጃዎችን እንዲሁም እንዲስፋፉ የተደረጉ መልካም ተሞክሮወችን የሰፉ ስለመሆናቸው መከታተል፤

**የሚንከታተላቸው መ/ቤቶች ለም/ቤቱ በቀጥታ በቃል መልስ የሚሰጡበት ጊዜ**

- ኮሜቴው ካለው ክትትል እና ህብረተሰቡ ከሚያነሳቸው አንገብጋቢ ጉዳዩች እንዲሁም በሚሰጡ ግብረ መልሶች መሰረት ተግባራዊ የማያደርጉ አካላትን ለምክር ቤቱ ወይም እንደ ጉዳዩ አስፈላጊነትና ክብደት በቋሚ ኮሜቴ ደረጃ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ እና የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ለምክር ቤቱ አባላትም ሆነ ከሕዝብ የሚሰበሰቡ አንገብጋቢና ወቅታዊ ጥያቄዎች በተለይም የምክር ቤት አባላት ወደ መረጣቸው አካባቢ በሚሔዱበት ወቅት ክህዝብ የተነሱ ማህበራዊ ነክ ጉዳዩች ላይ ኮሜቴው በመገምገም የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ምክር ቤት በመገኘት ወይም ለቋሚ ኮሚቴው በቃል መልስ እንዲሰጡ ሁኔታዎች ማመቻቸት
- ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አሰፈፃሚ መ/ቤቶች ለጥያቄ ሲጠሩ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት፣

**ግብ** 4 የሕዝብ ውክልና ተግባርን መወጣት

**<u>የሚጠበቅ ውጤቱ</u>:-** ለመራጩ ህዝብ የተሰጡ ተገቢና ወቅታዊ ምላሾች

- ቋሚ ኮሚቴው በሚከታተላቸው መ/ቤቶች ላይ በቀጥታና በተወካዮች አማካኝነት የሚነሱ ጥያቄዎችን በመቀበል ወቅታዊ ምላሽ መስጠት፤
- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው መስሪያ ቤቶች ሕዝቡን በታማኝነት በግልጽነትና ተጠያቂነት እያገለገሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሕዝብ ይፋ መድረክ ማዘጋጀት፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በድንገተኛ መስክ ምልከታ ችግሩ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- በሕዝብ እና በቋሚ ኮሚቴው የሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በሚመለከታቸው አካላት ምላሽ እንዲሰጥባቸው ማድረግና ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፤

**ግብ 5፡-** ቅሬታና ጥቆማን በመመርመር ምላሽ መስጠት

**የሚጠበቅ ውጤት**፡- የመጡ ጥቆማዎችና ቅሬታዎች ውጤታማ ምላሽ ማግኘታቸው

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- በቅድሚያ የቀረበው ጥቆማ ኮሚቴውን የሚመለከት መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን የማይመለከተው ጥቆማ ከሆነ ግን ኮሚቴውን እንደማይመለከት ጥቆማ ላቀረበው አካል ፈጥኖ ማሳወቅ፤
- የቀረበለትን ጥቆማ ተገቢ ጥቆማ ከሆነ ጉዳዩን ለሚመለከተው ንዑስ ኮሚቴ በመምራት ፍተሻ ተደርጎ ሀሳቡ ለቋሚ ኮሚቴው እንዲቀርብ ማድረግ፣ በቀረበው ሀሳብ ዙሪያ ውይይት ማካሄድና ለውሳኔ መድረስ፤
- የተወሰደውን ውሳኔ ሀሳብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ፤
- የቀረበው ጥቆማ ተአማኒ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ምላሽ የተገኘበት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ጥቆማ ላቀረበው አካል ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
- የሚታዩ ጉዳዮችን አፈ ጉባኤዎቹ እንዲያውቃቸው ማድረግ፤

**ግብ 6.** የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን መከታተልና ማስፈፀም

**የሚጠበቀዉ ውጤት፡-** ውጤታማ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አካታችነትና ተፈፃሚነት

**ዝርዝር ተግባራት:-**

- ሴክተር ዘለል ጉዳዮች ማለትም ስርዓተ ፆታን፣ ወጣቶችን፣ ኤች አይ/ቪ ኤድስን፣ የአካባቢ ጥበቃን፤ አካል ጉዳተኞችን፣ ኮሚቴው በሚከታተላቸው መ/ቤቶች በዕቅድ፣ በሪፖርታቸውና በተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው ማካተታቸውን ማረጋገጥ፤
- በመስክ ሥራ ወቅት በምንከታተላቸው መ/ቤቶች ዕቅድና ሪፖርት የተካተቱ ሴክተር ዘለል ጉዳዮች ተፈፃሚነት ማረጋገጥ፤
- በአመቱ መጨረሻ ላይ የተገኙ ውጤቶችን በመገምገም ለሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲደርሱ ማድረግ እና ከሌሎች ቋሚ ኮሜቴወች የተላኩ ቼክሊስቶችን የተከናወኑ ተግባራትን በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ፤
- ምክር ቤቱ የሚያሳድጋቸው ህፃናት ጉዳይ ያለው ስራ የተሻለ ቢሆንም ከሌሎች አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚስችል ሁኔታወችን መፍጠር፤
- የአካል ጉዳተኞችን፤አረጋዊያንን፣የወጣቶች ጉዳይ፤ኤች.አይ.ቪ.ኤድስና ስርአተ ምግብ ጉዳይን ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ከተጠሪ መ/ቤቶቻቸው ዕቅድና ሪፖርት አኳያ እንዲከታተሉ ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ መላክ እና አፈፃፀሙን በአመቱ መጨረሻ መከታተል፤

ግብ 7. መረጃ ማሰባሰብና ማደረጃት

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** ከቋሚ ኮሚቴው ተግባራት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አስፈላጊ የሆኑ የስራ መረጃዎችን፣ የተጠሪ መ/ቤቶችን እቅዶችና ሪፖርቶችን ወዘተ ፋይል አድርጐ በተፈለገ ጊዜ ማግኘት በሚችልበት አግባብ መደራጀት፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- በቋሚ ኮሚቴ በአመቱ የተሰሩ እቅዶች፣ሪፖርቶች፣የኮሚቴው ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች፣ በማስጠረዝ ዶክመንት ማድረግ፤
- ኮሚቴው የሚከታተላቸውን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ማንዋሎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ለኮሚቴው ስራ ግብዓት ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ሰነዶች ዶክመንት ማድረግ፤
- ኮሚቴው ከሚከታተላቸው መ/ቤቶች የተላኩ የአመቱ እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች በማደራጀት ማስቀመጥ፤

- የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስልጠናዎችንና የልምድ ልውውጦችን ዶክመንት ማድረግ፤
- የመስክ ጉብኝትና ቼክ ሊስቶችንና ዶክመንት ማድረግ፤
- ለአስፈፃሚ መ/ቤቶች በመስክም ሆነ ለእቅድና ለአፈፃፀም ሪፖርት የሚሰጡ ግብረ መልሶችን በተደራጀ ሁኔታ ማስቀመጥ፤
- ከጽ/ቤቱም ሆነ ከተለያዩ አካላት የሚላኩ ማስታወሻዎችና ደብዳቤዎች በማደራጀት እንዲቀመጡ ማድረግ፤
- የተያዙ ሰነዶች፣ እቅዶችና ግብረ መልሶች የኮሚቴውን ተግባራት ወዘተ...የያዘ መጽሄት በአመት ሁለት ጊዜ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፤

**ግብ. 8 የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ (የዴሞክራሲ ባህል ማጎልበት)**

**ዉጤት** 1. የተፈታ የመልካም አስተዳደር ችግሮች

**ውጤት** 2.በቋሚ ኮሚቴው ውስጥም የሰፈነ መልካም አሰተዳደር፣

**ውጤት** 3.ህብርብሄራዊ ሀገራዊ አንድነትን ማጠናከር

<u>**ዝርዝር አፈጻጸም**</u>

- ዴሞክራሲን በማስፈን ብልሹ አሰራሮችን ሌብነትን መከላከል ፤ እና ተጠያቂነት ማረጋገጥ
- የምክርቤቱን እሴቶች መተግበር
- ወድማማችንትና ፍቅር ያለው የተቀናጀ ስራ መስረት
- የሰራተኛውን የአሰራሩን እና የስራ ሰላም ማስፈን
- ተቋማት በእቅዳቸውና በሪፖርታቸው ዙሪያ ሰራተኞችን በንቃት ያሳተፉና የጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ስርአት የተዘረጋ መሆኑን መከታተል
- በተቋማት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች በነፃነት ሀሳባቸውን መግለፅ የሚችሉበትና ቅሬታዎቻቸው የሚስተናገዱበት ስርዓት መዘርጋቱን መከታተል

- በቋሚ ኮሚቴው በሚሰራቸው ማንኛውም ስራ በተለይም በስልጠና፣ በመስክ ጉዞ በአሳታፊነትና በግልጽነት ተግባራዊ መደረጉ፤
- በቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው ሁሉም ተቋማት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚፈታ መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ማካሄድ፤
- ቋሚ ኮሚቴው ውስጥ በስልጠና፣በመስክ ጉዞ እንዲሁም የውጭ ጉዞ ምልመላ ስራ ላይ ሁሉንም አባላት ባሳተፈ መልኩ ማከናወን፤

## 2.7. በማጠቃለያ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት፤

በዚህ ምዕራፍ የዓመቱ የስራ ማጠናቀቂያ በመሆኑ የአስፈፃሚውን የ2014 አመት በጀት እቅድ አፈጻጸምን ገምግመን ግብረ መልስ የምንሰጥበት ይሆናል፡፡ ሁሉንም ባሳተፈና ግልፅ በሆነ መንገድ የዓመቱን አፈፃፀሞችና የዓመቱን የቋሚ ኮሚቴ አፈፃፀሞችን ገምግሞ ልምድና ተሞክሮ መለየትና ለቀጣይ እንዲያገለገሉ ማድረግ ሲሆን በዋናነት የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.7.1. ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የማጠቃለያ ግምገማ ማካሄድ

<u>ዝርዝር አፈፃፀም</u>

- ስራዎች ሳይንጠባጠቡ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ እና ያልተፈጸሙ ተግባራት ያልተፈጸሙበትን ምክንያት በዝርዝር ማየት እና መፍትሔዎችን ማስቀመጥ፤
- በዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት የክትትል እና የቁጥጥር ድጋፍ እንዲሁም በተደራጀ ሁኔታ መፈጸሙን የማረገጋጥ፤መልካም አስተዳደር መስፈኑን ያስገኙትን ለውጥም እቅዱን ከማሳካት አኳያ ያለበትን ደረጃ በማረጋገጥ ከበጀት አመቱ አካያ የተከናወነውን ተግባር መገምገም፤
- በዓመቱ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች መቀመራቸውንና ወደ ሌሎች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፤
- የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም መረጃ በማደራጀት መያዝና የአፈፃፀም ሪፖርቱን ለም/ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ማሳወቅ፤
- የቋሚ ኮሚቴዉን 2015 እቅድ ማዘጋጀት እና የምንከታተላቸውን መስሪያ ቤቶች እቅድ መገምገም፤

**የአፈፃፀም አቅጣጫዎች**

- አሰራራችን እስትራቴጅን መሰረት አድርጎ የትኩረት አቅጣጫ በመለየት ቼክሊስትን በሚገባ በማዘጋጀት ይሆናል፣ ወደጥቃቅን ነገሮች በማትኮር ውጤት አልባ እንዳንሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡
- የቋሚ ኮሚቴ አባላት እርስ በርስ በመደማመጥ፣በመቀናጀት፣በፍቅርና በመተሳሰብ ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡
- ስራችንሁሉ ግልጽነትና ትብብርን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡
- ቋሚ ኮሚቴው በምንከታተላቸው መ/ቤቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሲያካሂድ በክትትልና ቁጥጥር አሠራር መመሪያን መሠረት በማድረግ ይሆናል፣የመስክ ምልከታ ተግባር በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ቼክሊስትና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶለት የሚፈፀም ይሆናል፤

## 2.7.2. **በአፈፃፀም ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች**

**ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች**

- ከቋሚ ኮሚቴው አንጻር ለስራው አዲስ መሆን፤
- በኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ ምክንያት የታቀዱ ስራዎችን ማከናወን የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡
- የምክር ቤቱ ስብሰባዎች መደራረብ ለቋሚ ኮሚቴው የስብሰባ ቀናት መስተጓጎል እና የቋሚ ኮሚቴ አባላት የመንጠባጠብ ችግር መኖር፤
- የምንከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና ሪፖርት አልፎ አልፎ መዘግየት፤
- በክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስፈፃሚ አካላት የሚሰጣቸውን ግብረ መልስ በግብአትነት አለመጠቀማቸው፤
- የመስክ ምልከታን በተመለከተ የሚዲያ፣ የትራንስፖርትና ሌሎች መሟላት የሚገባቸው ነገሮች በወቅቱ አለመቅረብ፤
- የቢሮ ጥገናዎችና ለሥራ የሚያስፈልጉ ግዥዎች በወቅቱ አለመከናወን፤

- በተለያየ ምክንያት የአቅም ግንባታ ስራዎች የመንጠባጠብ፤
- የአገራችን የፀጥታ ሁኔታ የመስክ ስራዎችን በታቀደው መሰረት እንዳይከናወን ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

**የመፍትሔ ሐሳቦች**

- የቋሚ ኮሚቴ አባላት የአቅም ግንባታ ስራዎችን በስልጠናዎችና የእርስ በርስ የመገነባቢያ መድረኮችን አጠናክሮ መሔድ፤ ስራውን ለመስራት የሚያስችል እውቀት መጨበጥ፤
- የትኩረት ዘርፎችን በደንብ በመዘጋጀት መያዝ፤የቋሚ ኮሚቴ ስራዎችን በተመለከተ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመከላከል የጤና ሚኒስቴር ባለሙያዎች በሚሰጡት መመሪያዎችና ም/ቤቱ በሚያስቀምጣቸው አቅጣጫ መፈፀም፤

- የተፈጠረውን አገራዊ ለውጥ በሚደግፍ እና በሚያግዝ አግባብ የክትትልና የድጋፍ ስርዓቱን ከመቼውም ጌዜ በበለጠ ሁኔታ አጠናክሮ መሔድ ወቅቱ የሚጠይቀው በመሆኑ ከአሁን በፊት ያገኘናቸውን ልምዶች በመጠቀም የበለጠ አጠናክሮ መሔድ ፤የተጠያቂነት እና የሕዝብን አመኔታ የምናገኝበትን አሰራር አጠናክረን መቀጠል፤
- የሚንከታተላቸው መ/ቤቶች ወቅቱን የጠበቀ እቅድና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ከመ/ቤቶቹ ኃላፊዎች ጋር ተወያይቶ መግባባት ላይ መድረስ፣ ክትትሉንም ማጠናከር፤
- የእቅድና የሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳዎችን ቀድሞ ለተቋማት ማሳወቅ፤
- ኮሚቴው የሚሰጠውን ግብረ መልስና በክትትልና በቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ የሚሰጣቸውን አስተያየቶች የምንከታተላቸው መ/ቤቶች እንደ ግብአትነት እንዲጠቀሙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ግብረ መልስን ተቀብሎ በማይፈፅም መስሪያ ቤቶች ላይ አሰፈላጊውን የማስተካካያ እርምጃ መውሰድ፤
- በጽ/ቤቱ መሟላት የሚገባቸው ግብአቶች እንዲሟሉ ቀድሞ ማሳወቅና መከታተል፣
- ወሳኝ ተግባራት ተለይተው እንዲፈፀሙ በመደጋገፍ መፈፀም፤

**የግምገማ፤ የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት**

- በቋሚ ኮሚቴ የሥራ ቀናት አባላት በሥራ ገበታቸው እንዲገኙ ክትትል ይደረጋል፤
- የንዑስ ኮሚቴዎች የስብሰባ ቀናት ሳይቆራረጡ መካሄዳቸው ክትትል ያደርጋል፤
- ንዑስ ኮሚቴው በሳምንት አርብ እና በወር አንድ ጊዜ ሥራውን ይገመግማል፤

- በወር አንድ ጊዜ የኮሚቴው ወርሃዊ የሥራ ሪፖርት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ለሚመለከታቸው የመንግስት ረዳት ተጠሪዎች ይቀርባል፤
- በአመት ሁለት ጊዜ አጠቃላይ የሥራ ግምገማ ይደረጋል፣ የተሟላ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ይላካል፤
- እርስ በራሳቸው የአቅም መገንቢያ ስርአት ይፈጥራሉ፡፡

## 2.8. <u>የጊዜ ሰሌዳ</u>

**የዝግጅት ምዕራፍ / ከጥቅምት - ህዳር 2014 ዓ.ም/**

- የኮሚቴው የ2014 እቅድ መከለስ አና ከአመራሩና ከአባላት ጋር የጋራ በማደረግ ማፅደቅ፣
- ➢ ንኡሳን ኮሚቴዎች የእራሳቸውን እቅድ ያዘጋጃሉ
- ➢ ከንኡስ ኮሚውቴ አባላት ጋር የጋራ በማድረግ ያጸድቃሉ
- ➢ በእቅዳችን ላይ በዝግጅት ምዕራፍ ይሰራሉ የተባሉ ስራዎች ይሰራሉ
- ➢ የዝግጅት ምእራፍ ስራዎችን ይገመገማል፤ ለቀጣይ ስምሪት ትምህርት ይወሰዳል፡፡
- ➢ ለሚከታተላቸው መስሪያ ቤቶችና ተጠሪ መስሪያ ቤቶች ትውውቅና የእቅድ ኦሪንቴሽን መስጠት፤

➢ የምንከታተላቸውን ምቤቶች እቅድ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

➢ **የተግባር ምዕራፍ**

- ➢ ከህዳር - ግንቦት 2014 ዓ.ም

**የማጠቃለያ ምዕራፍ**

➢ ከሰኔ 1 እስከ ሰኔ 30 /2014 ባለው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፡፡

## የጊዜ ሰሌዳ / የድርጊት መርሃ ግብር

### ሠንጠረዥ 1. የቋሚ ኮሚቴዉ የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

| ቀን | የሚከናወኑ ተግባራት | ፈፃሚ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 7/3/2014 | ቋሚ ኮሚቴው ከአባላት ጋር በመሆን የ2014 ዓ.ም እቅድ በመወያየት ያፀድቃል | ቋሚ ኮሚቴውና ባለሙያዎች | |
| 8/3/2014 | የፀደቀውን የቋሚ ኮሚቴ እቅድ ለተከበረው አፈ ጉባዔ ይላካል | ቋሚ ኮሚቴው | |
| 9/3/2014 | የቋሚ ኮሚቴ አመራሩና አባላት ከሚከታተሏቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎች ጋር የትውውቅ መድረክ ይኖራል | ቋሚ ኮሚቴውና የምንከታተላቸው አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች | |

## ሰንጠረዥ 2. መደበኛ የመስክ ምልከታን በሚመለከት የጊዜ ሰሌዳ

| ተ.ቁ | የመስክ ምልከታ የሚሄድባቸው ቦታዎች | የመስክ ምልከታ የሚካሄድበት ጊዜ | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወራት | የሚፈጅበት ጊዜ | የተሳታፊ ብዛት | |
| 1 | በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ፊንፊኔ ዙሪያ | ታህሳስ /2014 | 10 ቀናት | 13 አባላትና 8 ባለሙያ | ቋሚ ኮሚቴው |
| 2 | በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና<br>በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት | ታህሳስ /2014 | 20 ቀናት | 7 አባላትና 7 ባለሙያ | ቋሚ ኮሚቴው |
| 3 | በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | መጋቢት/2014 | 20 ቀናት | 7 አባላትና 7 ባለሙያ | ቋሚ ኮሚቴው |
| 5 | በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | ሚያዚያ/2014 | 20 ቀናት | 7 አባላትና 7 ባለሙያ | ቋሚ ኮሚቴው |

## ሰንጠረዥ 3.   የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና የተለያዩ ስልጠናዎች

| ተቁ | ሪፖርት ማድመጥ የሚካሄዱ ስብሰባዎች ወይም መድረኮች | ሪፖርት አቅራቢ ተቋም /ፈፃሚ አካል/ | የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | | | | | ጠቅላላ ተሳታፊ ብዛት | የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥቅምት | ህዳ | ታህ | ጥር | መጋ | ሚያ | ግን | ሰኔ | | አዳራሽ | ቃለ ጉባኤ | የድምፅ ቀረጻ | ካሜራና ዘጋቢ | projector | |
| 1 | የአለም አቀፍ ኤች አይቪ ኤድስ ቀንና የነጭ ሪቫን ቀን በግንዛቤ ማስጨበጫ ማክበር | የፌዴራል ኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት | | ህዳር 22ጠ -30 | | | | | | | 600 | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ | ✓ | የዓመቱን መሪ ቃል ምክኒያት በማድረግ ለምክር ቤት አባላት እና ለጽ/ቤቱ ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ |
| 2 | የጤናማ እናትነት ወርን ምክንያት በማድረግ በእናቶች ሞት ቅነሳ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት | ጤናሚኒስቴር | | | | ከጥር 1- እስከ 30 | | | | | 600 | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ | ✓ | ለምክር ቤት አባላት እና ለጽ/ቤቱ ሰራተኞችበአለቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ልገሳ ይፈጸማል |
| 3. | የማርች 8 ማክበር | ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | | | | | ✔ | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጋራ በመሆን |
| 4 | ስለ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን በሚመለከት የሚሰጥ ስልጠና | ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | | | | ✔ | | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታ የሚሰጥ ይሆናል |
| 5 | ስለቅርስ ምንነት፣ አያያዝና አጠባበቅ እንዲሁም አጠቃላይ ሁኔታን በሚመለከት | ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር | | | ✔ | | | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታየሚሰጥይሆናል |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ስለ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት አጠቃላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ | ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | | | ✔ | | | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታ የሚሰጥ ይሆናል |
| 7 | ስለጤና፣ ልማት አጠቃላይ ውይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ | ጤና ሚኒስቴር | | | ✔ | | | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታ የሚሰጥ ይሆናል |
| 8 | ስለመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭት የሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና | የመድሃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ | | | | | ✔ | | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታ የሚሰጥ ይሆናል |
| 11 | ስለ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር በወጣው አዋጅ አፈፃፀም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ | የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን | | | | | | | ✔ | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታ የሚሰጥ ይሆናል |
| 12 | በተለያዩ ስፖርታዊ ፌስቲቫሎችና ክንውኖች ላይ | ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር | | | | ✔ | ✔ | ✔ | | | አባላትና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በሙሉ | | | | | ✓ | መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ጊዜና ቦታየሚሰጥይሆናል |

ሰንጠረዥ 4. በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ በአካል ተጠርተው የሪፖርት ማድመጥ ኘሮግራም

| ተቁ | ሪፖርት ማድመጥ የሚካሄዱ ስብሰባዎች ወይም መድረኮች | የሚፈፀምበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | | | ጠቅላላ ተሳታፊ ብዛት | የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጥቅምት | ህዳ | ታህ | ጥር | መጋ | ሚያ | ግን | ሰኔ | | አዳራሽ | ቃለ ጉባኤ | የድምፅ ቀረጻ | ካሜራና ዘጋቢ | |
| 1 | የጤና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት | | | | ✔ | | | | | 70 | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ | |
| 2 | የሴቶችና ማህበራዊ ጉ/ሚር እና ተጠሪ ተቋማት | | | | | | ✔ | | | 50 | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ | |
| 3 | የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት | | | | | | ✔ | | | 60 | ✔ | ✔ | ✔ | ✔ | |

N.B ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ስንገመግም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ላይ በማተኮር ተጠሪ ተቋማትን አብሮ የመገምገም ስራ እንከተላለን

### ሰንጠረዥ 5.  በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚያቀርቡ አስፈፃሚ አካላት

| ተቁ | በቀጥታ ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ እንዲያቀርቡ የታቀደው ተቋም | ለምክር ቤቱ የሚያቀርበው ጉዳይ | የሚፈፀምበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥቅ | ህዳ | ታህ | ጥር | መጋ | ሚያ | ግን | ሰኔ |
| 1 | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | የ 6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | | | | ✓ | | | |
| 2 | የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | የ 9 ወር እቅድ አፈፃፀም | | | | | | ✓ | | |
| 3 | የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር | የ 6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | | | | ✓ | | | |

## የጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት የመደበኛ መስክ ምልከታ የበጀት መግለጫ

| ተ.ቁ. | የመስክ ጉብኘት የሚካሄድበት ቦታ | የቆይታ ጊዜ | የም/ቤቱ አባላት | | | ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች | | | የአባላትና የድጋፍ ሰጪ የአበል ድምር | የጉዞ አጠቃላይ ርቀት በኪ.ሜ | የነዳጅ መጠን (በሊትር) | የነዳጅ ዋጋ በሊትር | የተሸከርካሪ ብዛት | የነዳጅ ወጪ በብር | መጠባበቂያ የነዳጅ (10%) | አጠቃላይ የነዳጅ ወጪ በብር | ጠቅላላ ወጪ (አበል + ነዳጅ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | | | | | | | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 (1*2*3) | 5 | 6 | 7 (1*5*6) | 8 (4+7) | 9 | 10 (9/6) | 11 | 12 | 13 (10*11*12) | 14 (13*10%) | 15 (13+14) | 16 (8+15) |
| 1 | በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት | 20 | 7 | 515 | 72100 | 7 | 468 | 65520 | 137620 | | | | 3 | | | | |
| 2 | በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት | 20 | 7 | 535 | 74900 | 7 | 413 | 57820 | 132720 | | | | 3 | | | | |
| 3 | በአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | 20 | 7 | 595 | 83300 | 7 | 459 | 64260 | 147560 | | | | 3 | | | | |
| 4 | በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት | 20 | 7 | 590 | 82600 | 7 | 477 | 66780 | 149380 | | | | 3 | | | | |
| | ጠቅላላ ወጪ | | | | | | | | 567280 | | | | | | | | |

## የጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት መደበኛ የከተማ መስክ ምልከታ የበጀት መግለጫ

| ተ.ቁ. | የመስክ ጉብኝት የሚካሄድበት ቦታ | የቆይታ ጊዜ | የም/ቤቱ አባላት | | | ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች | | | የአባላትና የድጋፍ ሰጪ የአበል ድምር | የጉዞ አጠቃላይ ርቀት በኪ.ሜ | የነዳጅ መጠን (በሊትር) | የነዳጅ ዋጋ በሊትር | የተሽከርካሪ ብዛት | የነዳጅ ወጪ በብር | መጠባበቂያ የነዳጅ (10%) | አጠቃላይ የነዳጅ ወጪ በብር | ጠቅላላ ወጪ (አበል + ነዳጅ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | | | | | | | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 (1*2*3) | 5 | 6 | 7 (1*5*6) | 8 (4+7) | 9 | 10 (9/6) | 11 | 12 | 13 (10*11*12) | 14 (13*10%) | 15 (13+14) | 16 (8+15) |
| 1 | በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ፊንፊኔ ዙሪያ | 10 | 13 | 144 | 18720 | 8 | 180 | 1440 | 20160 | | | | 3 | | | | |
| | ጠቅላላ ወጪ | | | | | | | | 20160 | | | | | | | | |

## የጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት የድንገተኛ መስክ ምልከታ የበጀት መግለጫ

| ተ.ቁ. | የመስክ ጉብኝት የሚካሄድበት ቦታ | የቆይታ ጊዜ | የም/ቤቱ አባላት | | | ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች | | | የአባላትና የድጋፍ ሰጪ የአበል ድምር | የጉዞ አጠቃላይ ርቀት በኪ.ሜ | የነዳጅ መጠን (በሊትር) | የነዳጅ ዋጋ በሊትር | የተሽከርካሪ ብዛት | የነዳጅ ወጪ በብር | መጠባበቂያ የነዳጅ (10%) | አጠቃላይ የነዳጅ ወጪ በብር | ጠቅላላ ወጪ (አበል + ነዳጅ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | ብዛት | የቀን አበል | የአበል መጠን | | | | | | | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 (1*2*3) | 5 | 6 | 7 (1*5*6) | 8 (4+7) | 9 | 10 (9/6) | 11 | 12 | 13 (10*11*12) | 14 (13*10%) | 15 (13+14) | 16 (8+15) |
| 1 | ድንገተኛ መስክ ምልከታ1 | 15 | 13 | 540 | 105300 | 8 | 458 | 54960 | 160260 | | | | 5 | | | | |
| 2 | ድንገተኛ መስክ ምልከታ 2 | 15 | 13 | 575 | 112125 | 8 | 468 | 56160 | 168285 | | | | 5 | | | | |
| | ጠቅላላ ወጪ | | | | | | | | 328545 | | | | | | | | |

**የጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ  የበጀት መግለጫ**

| ተ.ቁ. | የምክክር መድረኩ አብይ ርዕስ | የቀን ቆይታ | የተሳታፊ ብዛት | መስተንግዶ ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በሰው | ጠቅላላ |
| 1 | ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር የሚደረግ የምክክር መድረክ | 1 | 110 | 500 | 55,000 |
| 2 | ከሴቶች፤ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የሚደረግ የምክክር መድረክ | 1 | 100 | 500 | 50000 |
| 3. | የባህልና ስፖርት ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር የሚደረግ የምክክር መድረክ | 1 | 100 | 500 | 50000 |
| | **በጠቅላላ የሚያስፈልግ በጀት** | | | | 155,000 |

**የጤና፤ማህበራዊ ልማት፤ባህልና ስፖርት ጉደዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት የአባላት የመስተንግዶ በጀት**

| ተ.ቁ | የአባላት ብዛት | የአንድ አባል የቀን ፍጆታ | የአንድ አባል የወር ፍጆታ (15 ቀናት) | የአንድ አባል የዓመት ፍጆታ (ለ8 ወራት) | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 13 | 60 | 900 | 7200 | 93,600 |
| | **ጠቅላላ ወጪ** | | | | 93,600 |

## አጠቃላይ አመታዊ በጀት

| ተ.ቁ | ተግባራት | አጠቃላይ ወጪ (በብር) | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | በ2014 በጀት ዓመት የመደበኛ የክልል መስክ ምልከታ | 567280 | |
| 2. | በ2014 በጀት ዓመት መደበኛ የከተማ መስክ ምልከታ | 20160 | |
| 3. | የድንገተኛ መስክ ምልከታ | 328545 | |
| 4. | ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ | 155,000 | |
| 5. | አባላት የመስተንግዶ | 93,600 | |

ድምር = 1,164,585

መጠባበቂያ (5%) = 58,229.25

**ጠቅላላ ድምር 1,222,814.25**